# በእውኑ የኢትዮጵያን ሕዝብ ቀድሞ ሊያምጽ የሚችል ሕዝብ ሊኖር ይገባ ነበርን?

ይሄይስ አእምሮ

## መግቢያ

ኢትዮጵያ ውስጥ በሰላም መኖር ከፈለግህ ማሟላት የሚጠበቅብህ ብዙ ነገሮች መኖራቸውን አትርሳ፡፡ በዋናነት ግን ገበያ አትውጣ፡፡ የምትገዛው ነገር አይኑርህ - እንዲኖርህም በፍጹም አትመኝ፡፡ የማንኛውንም ዓይነት አላቂም ሆነ ቋሚ ዕቃ ዋጋ አትጠይቅ፡፡ አትብላ፣አትጠጣ፣ አትልበስ፣ ቤትም እንዲኖርህ አትመኝ፤ ቀድሞውን ቤት ካለህም ሲያሻው በላይህ ላይ ይናድብህ እንጂ ለማደስ አታስብ፡፡ አምልኮት ቦታዎች አትሂድ - ግፋ ቢል የሚቀርብህ ‹ለትራንስፎርሜሽኑ ዕቅድ ተግባራዊነት ምዕመናን ከኢሕአዲግ ጎን ተሠልፈው አቅማቸው በፈቀደ እንደሚረባረቡ ብፁዕ አባታችን ያደረባቸውን ጸኑ ህመም (ይቅርታ- ያደረባቸውን እምነት ለማለት ነው) ለፋና ሬዲዮ ገለጹ› የሚለው የአባ ጳውሎስ ሃይማኖታዊ ካድሬ ስብከት ነው፡፡ የመንግሥትን የሀሰትና የበሬ ወለደ ቱሪናፋ የሚያራግቡ የኤፍምም ሆኑ መደበኛ የሬዲዮና የቲቪ ፕሮግራሞችን በምንም መንገድ አትከታተል፡፡ ባጭሩ የአእምሮ ጤንነትህን ከፈለግህ ያገኘሽውን እየቀመስክ ዝም ብለህ እንደከብት ኑር፡፡ በመንገድም ሆነ በገበያ ወይም በሌሎች የሕዝብ መሰባሰቢያ ሥፍራዎች በምታገኛቸው መሰል ዜጎችህ የአስተሳሰብና የአመለካከት መዛባት፣ የአነጋገርና የአለባበስ መንሻፈፍ እንዲሁም የአጠቃላይ ስብዕና ያልተለመዱ መገለጫዎች ምክንያት ለመበሳጨት በጭራሽ አትሞክር፤ ልታብድ ትችላለህና፡፡ ለቁጥር የሚያታክቱ ብዙ ሰዎች በተለይም ወጣቶች ኑሮኣቸውን እርግፍ አድርገው ጥለው ስለአውሮፓ ሻምፒዮንና ስለእንግሊዝ ፕሪሚየር ሊግ እግር ኳስ ጨዋታዎች እንቅልፍ አጥተው ሌሊቱን ሲጨፍሩ ብታይ ለምን እንደሆነ አትጠይቅ፤ መደበቂያ ዋሻቸው እንደሆነ ይነግሩህና የነሱ ካንተው ሊለይብህ ስለሚችል ልትበሳጭ ትችላለህ፡፡ ‹የኢትዮጵያ ሕዝብ በረሃብ አለቀ፤ በዴሞክራሲ ዕጦት ምክንያት ሰላምና ፍቅር ሀገራችንን ሊጎበኙ አልቻሉም› የሚል አጀንዳ አንስተህ ቢጤዎችህን ልታሳትፍ ብትሞክር የአርሴናል ወይም የቼልሲ ደጋፊ ‹ስለ ኢትዮጵያ ሕዝብ አንተን ምን ያገባሃል? ይልቅስ የኔ ቡድን ማንቼ በባርሴ ተሸንፎብኝ ጨጓራየ ጨሷልና አንድ ሁለት በለኝ› ቢልህ ማጣፊያው ሊያጥረህ ይችላል፡፡ ከዚህ ሁሉ ታዲያ ኢትዮጵያ ውስጥ በሰላም መኖር ከፈለግህ ሣር ባትግጥም ከብት ሁን፡፡ ከብት ሁን ስልህ ደንበኛ ከብት ሁን እንጂ እስስትና ጅብ ወይም ዓሣማና ተኩላ እንዳትሆን ተጠንቀቅ፡፡

## ሐተታ

የዛሬው ውሎየ ነው እንዲህ ብሶት በብሶት ያደረገኝ፡፡ በብሶት እንኳን መጀመር አልነበረብኝም፡፡ ግን ምን ይደረግ? ጥሎብን አንደበታችን እንደክርስቶስ በምሣሌ ሳይሆን በነገር የምንጀምር እየበዛን መጥተናል፡፡ መጨረሻችንን ያሳምርልን እንጂ ዘመኑ የለዬለት ኢዮባዊ የሥቃይና ራሔላዊ የዋይታ ዘመን ይመስላል፡፡ ለማንኛውም ለአሁኑ ይቅርታ አድርጉልኝ፡፡

ዛሬ ደመወዝ ተብየውን ነገር ወስድኩና ቤተሰቤን ሌላው ቢቀር የሽሮ አጃቢ አድርጌ ቲማቲም ራሴው ሠርቼ ለዩት ያለ የራት ግብር ላበላ አሰብኩና ወዳንዱ የአትክልት ግሮሠሪ ጎራ እላለሁ፤የኩዳዴ ጦም ሁለተኛው ሣምንት መጀመሩም ነው፡፡ አንድ ትልቅ ሰውዬም አብረውኝ ገብተዋል፡፡ እሳቸው ‹ያ ፋሮ ሽንኩርት ስንት ነው?› ይላሉ፤ ኪሎው 15 ብር ይላቸዋል ሠራተኛው፡፡ ይቀጥላሉ ሰውዬው - ‹ቃሪያስ?› ፤ 28 ብር ኪሎው ይላል መላሹ፡፡ ‹ሎሚስ?› ኪሎው 16 ብር - ከሩብ ኪሎ በታች ግን አይሸጥም ይላል አትክልተኛው፡፡ ሰውዬው የኔንም ጥያቄ እየጠየቁልኝ ስለሆነ በመልሱ ምክንያት የሚለዋወጠውን የፊታቸውን ገጽታ ጭምር በጥሞና መከታተሌን ይዣለሁ፡፡ እዛውንቱ ሰው በተለይ ኩዳዴ ገና ከመግባቱ በአትክልቶች ዋጋ ሰማይ መውጣት ከመጠን በላይ ከመደነቃቸው የተነሣ ስሜታቸውን ለመግለጽ ቃላት ሲከዱዋቸው አስተዋልኩ፡፡ እናም አሉ፤ ‹ፑ ፑ ፑ ፑ …›፡፡ ላመል ያህል

በተከፈቱት ወደፊት ያሞጠሞጡ ከንፈሮቻቸው በኩል ከሣንባቸው የሚፈተለከው የተቃጠለ አየር ቢያንስ የሦስት መንግሥታዊ ሥርዓቶችን የሕዝብ ኢኮኖሚያዊ ሕይወት በማነጻጸር የአሁኑን በመቅሰፍትነት ደረጃ ያስቀመጠ መሆኑን ስድስተኛው የስሜት ሕዋሴ ሹክ አለኝ፡፡ የሰውዬው ስሜት የቋንቋን ጎልውና ከመጤፍ ባለመቁጠር የሠራ ጅስማቸውን በወያኔ ወለዱ የኑሮ ውድነት የሣማ ግርፊያ ሲያንዘረዝረው ስመለከት እኔም በተመሳሳይ ስሜት ውስጥ ነበርኩና ሣቁን መቆጣጠር አቅቶኝ እንደማሽላዋ እያረርኩ ለቀቅሁት፡፡ የኔን ክትትል አላጤኑም ነበርና ደንገጥ በማለት ወደኔ ዞሩ፡፡ በሌላ ነገር እንዳይጠራጠሩኝ ወዲውኑ በራሴው ‹ራዳር ውስጥ› አስገብቼ ማናዘዜን ቀጥልኩ፡፡ ብዙ አወራን፡፡ ያለፈን ቢያወሩት ከንዴትና ቁጭት በስተቀር ዋጋ ስለሌለው በጀመርኩት የዕለቱ ገጠመኝ ትንሽ ልቀጥል፡፡

ጦሙ በገባ በሦስተኛው ቀን አካባቢ ቲማቲም አሰኘኝና ሎሚ ልግዛ ብል የሕጻን ልጅ ፍሬ ዘር የምታህለዋን ዕርም እምታህል ያልባለቀች ሎሚ አንድ ብር ይሉኛል፡፡ አምሮቴን ለመክላት ሌላ አማራጭ ስላልነበረኝ ገዝቼ ወስጄያት በተዘጋጀው ቲማቲም ላይ ልጨምቃት ብሞክር ጠላታችሁ ድርቅ ይበል ጠብ የሚል ነገር አልነበራትም፡፡ እግዚሃር ያሳያችሁ ዋጋዋ ግን አንድ ብር! በአንድ ብር ቁና ሎሚ እንዳልተገዛ ጢጠር እምታህል ደረቆቻ ሎሚ በአንድ ብር ይገዛ ጀመር፡፡

ይህን የምለው ችግራችን የሎሚና የሰላጣ ጉዳይ ሆኖ እንዳልሆነ ይገባኛል፡፡ እዩዬም ሲደላ ነውና ዛሬ የአብዛኛው ኢትዮጵያዊ ችግር የ‹ቅንጦቱ› ቲማቲም ሳይሆን ወስፋቱን የሚሸነግልበት ደረቅ ቆሎ ማጣቱ ነው፡፡ በአንጻራዊ ሁኔታ ከአብዛኛው ደሞዝተኛ በተሻለ የምንከፈለው የዱሮዎቹ ‹ንዑስ ከበርቴዎች› የዛሬዎቹ የወያኔ ሰለባ ምንዱባን ዜጎች እንዲህ ቲማቲም እንኳን ብርቅ ሲሆንብንና በደሞዝ አካባቢ የምንመገበው የክት ጮማ ሲሆንብን ሲቃጣው ሌላውማ እንዴቱን ያህል ይቸገር ይሆን? ይህን ተጠየቃዊ አመክንዮ አጉልቼ ላሳይ ስለፈለግሁ ነው እንግዲህ ይህን ተራ የሚመስል ነገር ግን ዕለታዊ ኑሮኣችንን በሚመለከት ከፍተኛ አንድምታ ያለውን የቲማቲም ጣጣ ያነሳሁት፡፡ ዛሬ ጊዜ ሥጋውንና ሌላውን ተውትና ቲማቲምና ሽሮም እንደብርቅ የሚቆጠርባቸው ኢትዮጵያውያን ቤቶች ሚሊዮኖች ናቸው፡፡ በሌላ በኩል ወያኔዎችና የወያኔዎች የሆኑ ጎሲናቢስ ዜጎች የሀገር ሀብት እየመዘበሩ እንዴት በመሰለ የተንደላቀቀ ሕይወት ውስጥ እንደሚገኙ እናውቃለን፡፡ በትምህርት ኤ ቢ ሲ ዲን ያልለዩ፣ በሙያ ረገድ አንዳችም የዕጅ ጥበብም ይሁን በጉልበት የሚከናወን ሙያ ባለቤቶች ያልሆኑና ከመብላትና መጠጣት፣ ቀን ከመተኛትና ሌት ከመዘሞት በስተቀር ምንም ዓይነት ለሀገር የሚጠቅም ልምድና ችሎታ የሌላቸው ወፍ ዘራሽ ዜጎች የወያኔው ሥርዓት በዘረጋላቸው የሙስና መስመር በመሠግሠግ የሀገሪቱን አንጡራ ሀብት ሙልጩን እያወጡት ናቸው፡፡ ሃይ ባይ የሌላቸው መሆናቸው የልብ ልብ እየሰጣቸው በየቀኑ ሚሊዮኖች በቁማቸው በኢኮኖሚ ወደ ወረደ መቃብር ሲወርዱ እነሱ ባልደከሙበት ሀብት እየተንፈላሰሱ ይሠራቻውን የሚያሳጣቸው ብልሹዎች ናቸው፡፡ እናም ኢትዮጵያ ውስጥ ሕዝቡ አሁንና አሁን ብቻ ካላመጻና እነዚህን መዥገሮችና ትኋኖች ከሰውነቱ ነቅሎ ካላፈረጠ የዛሬው ሕይወታችን ብቻ ሳይሆን ሀገራችን እንደሀገር የመቀጠልዋ ዕድል ራሱ በእጅጉ አሳሳቢ ነው፡፡

ሁሉም ጭቁን ዜጋ በየመንገዱ፣ በያካባቢው፣ በየዕድሩ በየሰንበቴው … ሲበሳጭና እጁን እያወራጨ ፀጉሩን እየነጨ እንደዕብድ ብቻውን ሲያወራ ታያላችሁ፡፡ ይመስለኛል - አንድ ያጣው ትልቅ ነገር አሰባሳቢ ኃይል ሳይሆን አይቀርም፡፡

ቅድም አካባቢ እንዲሁ አንድ ዕቃ ልገዛ ወደአንድ የሕንጻ መሣሪያዎች መሸጫ ሱቅ ጎራ ብዬ ነበር፡፡ አንዱ ሰውዬ የገዛው ምሥማር - ሊያውም ከሦስትና ከአራት ምሥማሮች አንዱ ብቻ የሚሠራ የተልፈሰፈሰ የወረቀት ምሥማር - ዋጋው ካለቅጥ አሻቅቦበት ኖሮ ፀጉሩን ሲነጭ አገኘሁት፡፡ ሻጭዋ ተቀጣሪ ሴትም ‹በሁሉም የመጣ ነው፤ ምን ይደረግ? እስኪያልፍ ቻል ማድረግ ነው- የኔ ጌታ!› እያለች ማጽናናትዋን ይዛ ነበር፡፡ የሚጽናና ሲገኝ አይደል ለዚያውስ? እንዲያውም እንዲ ስትለው ሰውዬው እዬወበራ ሄደ፤ ብሶቱ ይበልጥ ገነፈለ፡፡ …

ሰውዬው የጠቀሰው ሌላ አንድ ነገር ግን ጆሮዬን ይበልጥ አጓጓው፡፡ ሰሞኑን ‹አዲስ ልሣን› የተባለ የወያኔ ጋዜጣ ሊገዛ ወደማዘጋጃ ቤት ሄዶ ነበር - እሱው እንደነገረን፡፡ ጋዜጣውን በዋጋው እንዲሸጡለት ሲጠይቅ አባል ባለመሆኑ ለሱ እንደማይሸጥለትና ከሌሎች

ቀድመው ከገዙ መግዛት እንደሚችል ይነገረዋል፡፡ እነዚያ አባላት የተባሉት ጋዜጣውን የሚሸጡት ግን - አሁንም ሰውዬው እንዳለው - 60 እና 70 ብር በሚደርስ ከፍተኛ ገንዘብ ነው፡፡ በነገራችን ላይ ጋዜጣው የሚነበብ ቁንጅ ነገር ይዞ ሳይሆን የጨረታና የኮንዶምኒየም ዕጣዎችን የመሳሰሉ መረጃዎችን ስለሚይዝ ነው፡፡ የውድነት ጊዜውም ያን መሰል ወሬ በሚያትምበት ወቅት ነው፡፡ ሰውዬው ያኔ በንዴት ፎግልቶ ‹እኛስ ዜጎች አይደለንም ማለት ነው? ኢትዮጵያዊ አይደለንም እኛስ? እኩል መብት የለንም ማለት ነው?› ብሎ እንደተናገረና እንዳስደነገጣቸው አንዱ ሠራተኛ እንዲያውም ራሱን ይዞ (በሀፍረት) ዘወር እንዳለ ነገረን፡፡

## ማጠቃለያ

ጥሩ ጅምር ነው - የሰውዬው፡፡ ለመብት መከበር ሁሉም ቢያንስ ይቺን ታህል ቢንቀሳቀስ (ቢፎገላ) እስካሁን የተወሰኑ ድሎች ባለቤቶች ልንሆን እንችል ነበር፡፡ ሌላው ቢቀር ማንም የወያኔ ባለሥልጣን ሕዝቡን እንደተናጋሪ እንስሳ እየቆጠረ በላያችን ላይ ሊፈነጭብን ባልቃጣ፡፡ እርግጥ ነው - እንደመናገር ቀላል የለም፡፡ የአፍ አቀበት የለውም መባሉም ለዚህ ይመስላል፡፡ ከርዕሴ ጀምሬ ለመብት መከበር ሲባል ማመጽ ተገቢ መሆኑን በተዛዋሪም ይሁን በቀጥታ የምጠቁመው እንዳሁኑ ከሰው በታች ሆነን ከመኖር ይልቅ ለመብታችንና ለነጻነታችን በአንድነት ሆ ብለን ከተነሣን የማይቻለን ነገር እንደማይኖር ለማሳሰብ እንጂ በነጻነትና በባርነት መካከል ያለውን ድልድይ ሰባብሮ በመጣል እውነተኛዋን ነጻነት ለመቀዳጀት ትልቅ ዋጋ እንደሚጠይቅ አጥቼው አይደለም፡፡ ያን የምናደርገው ግን እኛም የመኖር መብት ስላለንና መኖርም ስላለብን እንጂ እነመለስ ዜናዊና ግብረ በላዎቹ ያላቸውን እንደኛው የመኖር መብት ለመገደብ ወይም እነሱ በኛ ላይ እንደሚያደርጉት ከነአካቴው ጎልውናቸውን ለመጨፍለቅ እንዳልሆነ ግልጽ ነው፡፡ ክፋትን በክፋት መመለስ ሃይማኖታዊም ሞራላዊም የመልካም ሥነ ምግባር መገለጫ ባለመሆኑ የሚሠራብንን ግፍ ከማስቆምና ጥፋተኞችን በሠሩት ጥፋት ልክ ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድባቸው ከማድረግ ባለፈ የብቀላና የ‹ዐይንን ለዐይን፤ ጥርስን ለጥርስ› ኦሪታዊ ሕግ የምንተገብርም አንሆንም፡፡ እንዲህ ከሆነ ሞኞች ባንድኛቸው ቤት በእንግድነት ተገናኝተው ሊሰነባበቱ ሲሉ ሲሸኛኙ እንደሚያድሩት እኛም ግፍና በደልን ስንመላለስ እስከዓለም ፍጻሜ በውሃ ቅዳ ውሃ መልስ ልንኖር ነው ማለት ነው፡፡

እዚህ ላይ በተጓዳኝ መገንዘብ ያለብን ሌላ ዋና ጉዳይ በተናጠል ወይም በተወሰነ አነስተኛ የሰው ኃይል የሚደረግ የመብት ማስከበር ጥያቄና የትግል ጥሪት በአምባገነኖች በቀላሉ የሚቀለበስ መሆኑን ነው፡፡ ሁላችን በአንድ ልብ ለአንድ ዓላማ ከተነሣን ግን በቀላል መስዋዕትነት የፈለግነውን ድል መጨበጥ እንችላለን፡፡ መስዋዕትነትን ፈርተን ወይም በሌሎች መስዋዕትነት ከግፍ አገዛዝ ቀምበር ለመውጣት ፈልገን ከጋርዮሹ የትግል ማዕድ ወደኋላ የምናፈገፍግ ከሆን ግን ልክ እንደስካሁኑ ባለንበት መርገጥም ህልም እየሆነብን የቁልቁል ሩጫችንን በበለጠ ፍጥነት ማጧጧፋችንን እንቀጥላለን፡፡ ያ ደግሞ ጨቋኞች ስንጥቅ የሚያተርፉበት እኛ ደግሞ ያለችንን እንጥፍጣፊ ሁሉ ሳትቀር አሟጥጠን ጨርሶውን የምንከስርበት አጋጣሚ ከመሆን አይዘልም፡፡ እንደስካሁኑ ብዙ ተጎድተናል፤ ዝምታችን የመቃብር ዓይነትና አስፈሪም ሆኖ እስካሁኒትዋ ደቂቃ ዘልቋል፡፡ ይህ እውነት ይመስለኛል፡፡

ከታሰበበት አሁንም ይደርሳል፡፡ ፈረንጆቹ ‹ጭራሹን ከመቅረት ዘግይቶም ቢሆን መድረስ› እንደሚሉት የረፈደብን መስሎ አይሰማን፤ ጭራሹን ተስፋ በሚያስቆርጥ ሁኔታ አልረፈደብንም፡፡ በግልም በቡድንም እየተደራጀን ባገኘነው አጋጣሚ ሁሉ የግልና የወል መብቶቻችንን ለማስከበር ከቆረጥን ወያኔ ምንም ሊያደርገን አይችልም፡፡ የሕዝብ ኃይል አስፈሪ ግርማ ሞገስ አለው፡፡ የሚያስፈራው ግን መብታችንን እንደኤሣው ባልረባ ነገር ሳንሸጥ በጋራ ለጋራ ነጻነት እስከመጨረሻው የታገልን እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ ለማንኛውም ፈጣሪ ይርዳን፡፡ እኔም ከወር በፊት ወደማላገኘው ቲማቲሜ ልሂድ፡፡ እንግዲህ ዋ ብሎ ጉርስ አይቀር፤ ምን ላድርግ? ለማኝኛውም አስተያየት፤ yiheyisaemro@gmail.com